# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# የቤተክርስቲያን ውልደት

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest, Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



ኢየሱስ ሲሞት ፣ ሲፈሩ የነበሩ ተከታዮቹ ተደበቁ፡፡ ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ፣ ለደቀመዛሙርቱ ራሱን ገለጠ፡፡ ኢየሱስ ሕያው ነበረ፡፡ ነገር ግን ፣ ኢየሱስ እነርሱን ሊለያቸው ወደደ ፤ ወደ ሰማይ ሊመለስ ፣ ሁልጊዜ ከሚኖርበት ከአባቱጋ ሊሆን፡፡



ከመሔዱ አስቀድሞ ፣ ኢየሱስ
ለተከታዮቹ መንፈስ ቅዱስን የእነርሱ
ረዳትና አጽናኝ አድርጎ እንደሚልክላቸው
ቃል ገባላቸው፡፡ ሰዓቱ ቀርቧል ! ኢየሱስ ከመሔዱ ጥቂት
ቀናት አስቀድሞ ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ መጣ፡፡

በዚህ መልኩ ሆነ። አንድ መቶ ሃያ የሚሆኑ ተከታዮቹ ቤት ውስጥ ሆነው ይጸልዩ ነበረ። በድንገት ፣ ቤቱ በታላቅ አውሎ ንፋስ ተሞላ።



የተከፋፈሉ የእሳት ነበልባሎች በሰዎች ላይ አረፉ፡፡ ኢየሱስ ቃል እንደገባላቸው ፣ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፡፡



በመንገዶቹ ላይ ሁሉ ፣ የኢየሱስ ተከታዮች ተምረው የማያውቁተን ቋንቋ ይናገሩ ጀመር፡፡ ኢየሩሳሌምን የሚጎበኙ ሰዎች የኢየሱስ ተከታዮች የእግዚአብሔርን ድንቅ ስራ በብዙ ቋንቋዎች ሲናገሩ ሰሙአቸው፡፡ ጎብኚዎቹ እጅግ ተደነቁ፡፡ “ይሄ ምንድነው” ብለው ጠየቁ፡፡ ሌሎችም “በወይን መጠጥ ሰክረዋል” ብለው አፌዙ፡፡



ነገር ግን ጴጥሮስ ፣ “እነዚህ ሰክረው አይደለም ፤ ……ይሔ በነብዩ በኢዩኤል እንደተባለ ነው…” ከዚያም ጴጥሮስ ከብዙ አመታት አስቀድሞ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣና ሕዝቡን እንደሚባርክ እና እንደሚረዳ ተስፋ መስጠቱን አስታወሳቸው፡፡



ጴጥሮስም ሰዎቹን ከኃጢያታቸው ዘወር እንዲሉና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ ነገራቸው፡፡ “.....የመንፈስ ቅዱስንም ተስፋ ታገኛላችሁ፡፡” አላቸው፡፡ ሶስት መቶ ሺህ የሚሆኑ ሰዎች ታዘዙ፡፡ የኢየሱስ አምላኪዎችም በመሆን ደቀመዛሙርቱን ተቀላቀሉአቸው፡፡ ጊዜው ሲሔድ ፣ ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በማፍሰስ የጀመራት ቤተክርስቲያን ውስጥ ይጨመሩ ነበረ፡፡



መንፈስ ቅዱስ ኃይሉን ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ሕይወት ያመጣ ነበረ፡፡ አንድ ቀን ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ በጸሎት ሰዓት ወደ ቤተመቅደስ አብረው ይወጡ ነበረ፡፡ ሽባ የሆነ ለማኝ በቤተመቅሱ መግቢያ ላይ ተቀምጦ ነበረ፡፡ ዮሐንስንና ጴጥሮስንም ገንዘብ ይለምናቸው ነበረ፡፡





ጴጥሮስም እንዲህ አለው ፣”
ገንዘብና ወርቅ የለንም ፣ ያለንን ግን
እንሰጥሃለን ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ
ክርስቶስ ስም ተነሳና ተመላለስ፡፡”
ከዚያም ፣ ተነስቶ ፣ እየተረማመደና
እየዘለለ ፣ እግዚአብሔርን እያመሰገነ
ወደ መቅደስ ገባ፡፡

እጅግ ብዙ ሕዝብም ተሰበሰበ፡፡ በተአምራቱም ተገረሙ፡፡ ጴጥሮስም ሽባውን የፈወሰው የእግዚአብሔር ኃይል እንጂ የእርሱ ስራ አለመሆኑን ነገራቸው፡፡ ጴጥሮስም አይሁዳዊያኑን እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሙታን መካከል እንዳነሳው ሲነግራቸው ፣ የቤተመቅደሱ አለቆች በመናደድ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ያዙአቸውና በወህኒ አኖሩአቸው፡፡ ነገር ግን ፣ አምስት ሺህ የሚሆኑ ሰዎች በኢየሱስ አመኑ፡፡



በሚቀጥለውም ቀን ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ በመቅደስ አዛዦች ፊት ቆሙ።
ገዥዎቹም ፣ “በምን ኃይልና በማን ስም ነው ይሔንን ያደረጋችሁት;” ብለው ጠየቁአቸው። በመንፈስም ተሞልቶ ፣ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል መለሰ።
“በናዝሬቱ ኢየሱስ ስም ፣ እናንተ በሰቀላችሁት ፣ እግዚአብሔር ከሙታን መካከል ባስነሳው፣ በእርሱ ይሔ ሰው በእናንተ ፊት ተነስቶ ቆሟል።”





ጴጥሮስም ምንም ሳይፈራ ንግግሩን ቀጠለ ፤ “....እኛ ልንድንበት የምንችል ምንም አይነት ስም ከምድር በታች በሰው መካከል የለም” አላቸው፡፡ በኢየሱስ ለማመን ስላልፈለጉ ፤ ገዥዎቹ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ማስፈራራታቸውን ቀጠሉ፡፡ “ከዚህ ሰዓት ጀምሮ በኢየሱስ ስም ለማንም እንዳትናገሩ” ብለው አስጠነቀቁአቸው፡፡

ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ለመሚገት አንድ ወቅት ይፈራ ነበረ፡፡ ነገር ግን ያ የሆነው



መንፈስ ቅዱስ ሳይመጣ አስቀድሞ ነበረ፡፡ አሁን ማንም እርሱን ሊያስፈራራው አይችልም፡፡ ጴጥሮስና ዮሐንስም መለሱ ፣ "ፈራጆች ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ልክ የሆነውን ነገር ሁሉ እንጂ እናንተን ልንሰማችሁ አንችልም፡፡ የሰማነውን ያየነውን ከመናገር ውጪ ምንም ማድረግ አንችልም፡፡"

ከብዙ ማስፈራሪያ
በኋላ ፣ ገዢዎቹ
ጴጥሮስንና ዮሐንስን
ፈቱአቸው፡፡ ጀግናዎቹ
የእግዚአብሔር አገልጋዮች
አብረዋቸው ለነበሩት ሁሉ
ስለ እስርና ስለፍርድ
ነገሯቸው፡፡ ከዚያም ታላቅ
የጸሎትና የምስጋና ጊዜ
አደረጉ፡፡ እንደገናም ፣
የእግዚአብሔር መንፈስ
የእርሱን ሕዝብ በኃይል ሞላ ፤
ታናሽ የነበረችው ቤተክርስቲያንም
እጅግ ታድግ ጀመረ፡፡



የቤተክርስቲያን ውልደት

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ሐዋሪያት ስራ 1 -4

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

# መጨረሻ

55

60

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16